# ታሪኮች

(ሊዎ ቶልስቶይ)

ውርስ-አስተኔ ትርጉም

(እሱባለው አማረ)

# ሦስቱ ፈለጎች

---

በደቡብ አሜሪካ ቀደምት ጎሳዎች የሚነገር አፈ-ታሪክ፡-

እግዚአብሔር ሰውን ፈጠረ፡፡ ሰውም በምድር ላይ ለመኖር ሥራ፣ መጠለያ፣ አልባስ፣ ምግብ አያስፈልገውም ነበር፡፡ እግዚአብሔር የፈጠራቸው ሰብዓት በሙሉ የሚሞቱበትን ቀን ያውቁ ነበር፡፡ እስከ መቶ ዓመትም ይኖሩ ነበር፡፡ ህመም ምን እንደሆነም አያውቁም ነበር፡፡

ከአዝማናት በአንዱ፣ እግዚአብሔር ወደ ምድር ወረደ፡፡ የሰው ልጆች በጥልቅ ኀዘን እየኖሩ ጠበቁት፡፡ በሰው ልጆች መሀል ሠላም አልነበረም፡፡ ሁሉም ስለራሱ አብዝቶ ይጨነቅ ነበር፡፡

እግዚአብሔር አምላክም ለራሱ እንዲህ አለ፡- "ይሄ ሁሉ የሆነው የሰው ልጆች ያለማንም እርዳታ ራሳቸውን ችለው መኖር በመቻላቸው ነው፡፡" የሰው ልጆች ያለሥራ መኖር እንዳይችሉ ኪርዮስ ጌታ አዘዘ፡፡ ሆነም፡፡ የሰው ልጆችም ከውርጭና ከሀሩር ለመጠለል መጠለያ መቀለስ ጀመሩ፡፡ ከረኀብ ለመሸሽ አዝርዕት መዝራት፣ ፍራፍሬ መልቀም ለመዱ፡፡

"ሥራ የሰው ልጆችን ያቀራርባል፡፡ የሰው ልጅ መጠለያውን ብቻውን መቀለስ አይቻለውም፤ የሰው ልጅ ሰብልን ብቻውን ዘርቶ ብቻውን መሰብሰብ አይቻለውም፤ የሰውን ልጅ አልባሳቱን ብቻውን ፈትሎ ብቻውን መሸመን አይቻለውም፡፡ የሰው ልጆች በሕብረት በሠሩ ቁጥር፣ የተሻለ ምርት ይኖራቸዋል፣ የተሻለ ሕይወት ይኖራሉ፣ በመካከላቸው ፍቅርና ሠላም ይሰፍናል፡፡" ሲል አዶናይ ጌታ አሰበ፡፡

በጊዜ እንዝርት ላይ ምዕት ዘመናት ተሽከረከሩ፡፡ የሰው ልጆች በደስታ እየኖሩ መሆናቸውን ይመለከት ዘንድ እግዚአብሔር ዳግም ወደ ምድር ወረደ፡፡ በሰው ልጆች መሀል ከምንጊዜውም በላይ ሠላም ርቆ ጠበቀው፡፡ የሰው ልጆች በትናንሽ ቡድኖች ተከፋፍለው ይናቆሩ ነበር፡፡ አንደኛው ቡድን የሌላኛውን ቡድን የሥራ ፍሬ ለመንጠቅ ይሞክር ነበር፡፡

እግዚአብሔር አምላክ አዘነ፡፡ "የሰው ልጅ የሚሞትበትን ቀን አይወቅ፡፡ በማንኛውም ሰዓት ነፍሱ ከሥጋው ትላቀቅ፡፡" አለ፡፡ ሆነም፡፡

“የሰው ልጅ በማንኛውም ሰዓት ሊሞት እንደሚችል እያወቀ፣ ለጊዜአዊ ጥቅም ብሎ ኃጥእ ተግባር አይፈፅምም፡፡” ሲል እግዚአብሔር አምላክ አሰበ፡፡

ነገር ግን እግዚአብሔር ያሰበው ሳይሆን ቀረ፡፡ የሰው ልጆች እርስ በእርሳቸው መገዳደል ጀመሩ፡፡ ሞትን ለማስፈራሪያት በመጠቀም ኃያላን የድኩማንን ጉልበት በዘበዙ፡፡ በሰው ልጆች መሀል ጥላቻ ነገሠ፡፡ ሕይወት የኀዘን ከል ለበሰች፡፡

እግዚአብሔር አምላክ በሰው ልጆች መሀል ፍቅርና ሠላምን ያነግሥ ዘንድ ህመምን ፈጠረ፡፡ እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፡- “የሰው ልጆች ለህመም የተጋለጡ መሆናቸውን ካወቁ፣ ጤነኞች ህሙማንን ይረዳሉ፡፡ ይንከባከባሉ፡፡ በመካከላቸውም ፍቅርና መተሳሰብ ይሰፍናል፡፡” ህመምም በሰው ልጆች መሀል ፍቅርና ሠላምን ለማስፈን የተፈጠረ የመጨረሻው ፈለግ ሆነ፡፡

ህመም በሰው ልጆች መሀል መተሳሰብ ማንገሡን ይመለከት ዘንድ እግዚአብሔር አምላክ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ምድር ወረደ፡፡ የሰው ልጆች በጥልቅ የኀዘን ባሕር ውስጥ ተዘፍቀው ጠበቁት፡፡ ድኩማን ኃያላንን ያስታምሙ ነበር፡፡ ድኩማን በታመሙ ጊዜ ግን የሚያስታምማቸው አልነበረም፡፡ ድኩም ህሙማን በሽታ እንዳያስተላልፉ ይገለሉ ነበር፡፡ በሥራ የተዳከመ አካላቸው በሽታን የመቋቋም አቅም አልነበረውም፡፡

እግዚአብሔርም “የሰው ልጅ ሥራ፣ ሞትና ህመም የደስታና የፍቅር ምንጮች መሆናቸውን ካላወቀ፣ በመከራ ይማር፡፡” ብሎ ላይመለስ ወደ ጽርሐ አርያም ወጣ፡፡

ከዘመናት በኋላ ጥቂት የሰው ልጆች ይህንን ተረዱ፡-

ሥራ፡- የአለቃና የምንዝር፣ የባሪያና የጌታ፣ የአገልጋይና የተገልጋይ ግንኙነት ሳይሆን በሰው ልጆች መሀል መቀራረብንና ደስታን የሚፈጥር የጋርዮሽ ግብር መሆኑን፡፡

ሞት፡- አንደኛው ሌላኛውን እያስፈራራ የሚገዛበት ሳይሆን እንያንዳንዱ ዘርዐሰብ ከእግዚአብሔር በውሰት የተሰጡትን ዓመታት፣ ወራት፣ ሳምንታት፣ ቀናትና ሰዓታት በፍቅርና በአንድነት ለማሳለፍ የተፈጠረ ክስተት መሆኑን፡፡

ህመም፡- በሰው ልጆች መሀል መከፋፈልንና መገለልን የሚፈጥር ሳይሆን መረዳዳትንና መተሳሰብን ለማንገሥ ከአምላክ የተሠጠ ሥጦታ መሆኑን፡፡

# የሦስት ዘመኖች ወግ

---

የአንድ መንደር ሕፃናት ከጥልቅ ሸለቆ ሥር ዕንቁላል የሚያህል የበቆሎ ፍሬ ወድቆ አገኙ፡፡ አንድ መንገደኛ ዕንቁላል የሚያህለውን በቆሎ ከሕፃናቱ ገዛው፡፡ወደ ከተማ ወስዶ ለንጉሡ ሸጠው፡፡

ንጉሡ በግዛቱ የሚኖሩ ጠቢባንን በሙሉ ወደ ቤተ-መንግሥት ጠራ፡፡ ዕንቁላል የሚያህለው በቆሎ ምን እንደሆነ እንዲለዩት አዘዘ፡፡ ጠቢባኑ ዕንቁላል የሚመስለውን በቆሎ ለበርካታ ቀናት አስተዋሉት፡፡ ምን እንደሆነ መለየት ግን ተሳናቸው፡፡

አንድ ቀን ያልተጠበቀ ክስተት ተከሰተ፡፡ ዕንቁላል የሚያህለው በቆሎ የቤተመንግሥቱ መስኮት መቃን ላይ እንደተቀመጠ፣ አንዲት ዶሮ በማንቁርቷ አነደነደችው፡፡ ሁሉም ጠቢባን የበቆሎ ፍሬ መሆኑን ተረዱ፡፡ ጠቢባኑ ይህንኑ ለንጉሡ ተናገሩ፡፡

ንጉሡ ተደነቀ፡፡ ዕንቁላል የሚያህል የበቆሎ ፍሬ መቼና የት እንደሚበቅል ያጣሩ ዘንድ ጠቢባኑን አዘዘ፡፡ ጠቢባኑ መጽሐፎቻቸውን አሰሱ፡፡ ዕንቁላል ስለሚያህል የበቆሎ ፍሬ የተጻፈ አንዳች ነገር አልነበረም፡፡ ጠቢባኑ ወደ ንጉሡ ተመልሰው እንዲህ አሉ፡-

“በመጽሐፎቻችን ውስጥ ዕንቁላል ስለሚያህል የበቆሎ ፍሬ የተጻፈ ነገር የለም፡፡ ንጉሥ ሆይ! ስለዚህ ጉዳይ ጭሰኞችን መጠየቅ ይኖርብዎታል፡፡ አባቶቻቸው ዕንቁላል ስለሚያህል የበቆሎ ፍሬ የተረኩላቸው ተረክ ሊኖር ይችላልና፡፡”

ንጉሡ የዕድሜ ባለጸጋ ገበሬ ተፈልጎ ወደ ቤተ መንግሥት እንዲመጣ ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ አንድ እርጅና በእጅጉ የተጫጫነው፣ ቡትቶ የለበሰና ጥርሶቹ የወላለቁ የዕድሜ ባለጸጋ ገበሬ ተፈልጎ ከንጉሡ ፊት ቀረበ፡፡ የዕድሜ ባለጸጋው ገበሬ በሁለት ክራንቾች እየታገዘ ወደ ንጉሡ ዙፋን አመራ፡፡

ንጉሡ የበቆለውን ፍሬ ለዕድሜ ባለጸጋው ገበሬ አሳየው፡፡ ነገር ግን የዕድሜ ባለጸጋው የዕይታ አድማስ የተዳከመ ነበርና ሊታየው አልቻለም፡፡ የበቆሎውን ፍሬ ከንጉሡ ተቀብሎ ዳሰሰው፡፡ ንጉሡ የዕድሜ ባለጸጋውን ጠየቀ፡-

“እንደዚህ ዓይነት የበቆሎ ፍሬ የት እንደሚበቅል ሊነግሩን ይቻላሉ? እንደዚህ ዓይነት በቆሎ ሸምተው ወይም በማሳዎ አብቅለው ያውቃሉ?”

የዕድሜ ባለጸጋው ጆሮዎች መስማት ያዳገታቸው ነበሩና፣ የንጉሡን ንግግር ዘግይተው ተረዱ፡፡

"በፍፁም!" የዕድሜ ባለጸጋው በመጨረሻ ምላሽ ሰጠ፣ "እንደዚህ ዓይነት የበቆሎ ፍሬ ዘርቼም፣ ሰብስቤም፣ ሸምቼም አላውቅም፡፡ በእኛ ዘመን የነበሩ የበቆሎ ፍሬዎች ልክ እንደ አሁኑ ዘመን የበቆሎ ፍሬዎች ትናንሾች ነበሩ፡፡ አባቴን ልትጠይቁት ትችላላችሁ፡፡ እንደዚህ ዓይነት የበቆሎ ፍሬ የት እንደሚበቅል ሰምቶ ይሆናል፡፡"

የዕድሜ ባለጸጋው አባት ተፈልጎ ከንጉሡ ፊት ቀረበ፡፡ በአንድ ክራንች እየታገዘ ወደ ንጉሡ ዙፋን አመራ፡፡ ንጉሡ የበቆሎውን ፍሬ አሳየው፡፡ የዕድሜ ባለጸጋው አባት የዕይታ አድማስ ገና ያልተዳከመ ነበርና የበቆሎውን ፍሬ በጥንቃቄ አስተዋለው፡፡ ንጉሡ ጠየቀ፡-

"እንደዚህ ዓይነት የበቆሎ ፍሬ የት እንደሚበቅል ሊነግሩን ይቻላሉ? እንደዚህ ዓይነት በቆሎ ሸምተው ወይም ከማሳዎ ሰብስበው ያውቃሉ?"

ጆሮዎቹ ከልጁ ጆሮዎች የተሻለ የመስማት ዐቅም ነበራቸው፡፡

"በፍፁም!" አዛውንቱ መለሰ፣ "እንደዚህ ዓይነት የበቆሎ ፍሬ ዘርቼም ሰብስቤም አላውቅም፡፡ በእኛ ጊዜ ገንዘብ መገበያያ ስላልነበር ምንም ነገር ገዝቼ አላውቅም፡፡ ሁሉም የራሱን አዝርዕት ይዘራል፡፡ በቸገረን ጊዜ ከሌሎች እህል እንወስዳለን፡፡ እንደዚህ ዓይነት በቆሎ የት እንደሚበቅል አላውቅም፡፡ በእኛ ዘመን የነበሩ የበቆሎ ፍሬዎች በዚህ ዘመን ካሉት የበቆሎ ፍሬዎች በመጠን የተለቁ ነበሩ፡፡ በዚህ ዘመን ካሉት የበቆሎ ፍሬዎች የበለጠ ዱቄት ይወጣቸው ነበር፡፡ ዕንቁላል የሚያህል የበቆሎ ፍሬ ግን ዓይቼ አላውቅም፡፡ ነገር ግን አባቴ በእነርሱ ዘመን ይበቅል የነበረው በቆሎ፣ በእኛ ዘመን ይበቅል ከነበረው የበለጠ መጠንና ምርት እንዳለው ሲናገር ሰምቻለሁ፡፡ እርሱን ብትጠይቁት ይሻላል፡፡"

የአዛውንቱ አባት ተፈልገው ከንጉሡ ፊት ቀረቡ፡፡

ያለ ክራንች እገዛ እየተራመዱ ወደ ንጉሡ ዙፋን አመሩ፤ ዓይኖቻቸው የጠሩ ናቸው፣ ጆሮዎቻቸው ያለ እክል ይሰማሉ፣ አንደበታቸው የተፍታታ ነው፡፡ ንጉሡ የበቆሎውን ፍሬ አሳያቸው፡፡ አዛውንቱ አያት የበቆሎውን ፍሬ ከንጉሡ ተቀበሉ፡፡

"እንዲህ ዓይነት በቆሎ ካየሁ ብዙ ዘመን ሆኖኛል፡፡" አዛውንቱ አያት ዕንቁላል ከሚያህለው የበቆሎ ፍሬ ጎርደው እየቀመሱ ተናገሩ፣ "በእጅጉ ተመሳሳይ ነው!"

“እንደዚህ ዓይነት በቆሎ መቼና የት ይበቅል እንደነበር ሊነግሩኝ ይችላሉ? እንደዚህ ዓይነት የበቆሎ ፍሬ ሸምተው ወይም ከማሳዎ ሰብስበው ያውቃሉ?” ንጉሡ ጠየቀ፡፡

አዛውንቱ አያት ምላሽ ሰጡ፡-

“በእኛ ዘመን እንደዚህ ዓይነት የበቆሎ ፍሬ በየ ቦታው ይበቅል ነበር፡፡ እንደዚህ ዓይነት በቆሎ ነበር ዘርተን የምንሰበስበው፡፡

ንጉሡ ጠየቀ፡-

“ከገበያ ትሸምቱ ነበር ወይስ ሁላችሁም ዘርታችሁ ትሰበስቡ ነበር?”

አዛውንቱ ፈገግ ብለው መለሱ፡-

“በእኔ ዘመን መግዛትና መሸጥ ኃጢአት ነበሩ፡፡ ገንዘብ ምን እንደሆነ አናውቅም ነበር፡፡ ሁሉም ሰው በቂ በቆሎ ነበረው፡፡”

“ማሳዎ የት ነበር? የትስ ነው እንደዚህ ዓይነት የበቆሎ ፍሬ ይዘሩ የነበረው?” ንጉሡ ጠየቀ

አዛውንቱ አያት መለሱ፡-

“ማሳዬ የፈጣሪ መሬት ነበር፡፡ ያረስኩት መሬት ሁሉ የእኔ ማሳ ነበር፡፡ መሬት ነጻ ነበር፡፡ መሬት ማንም ሰው የእኔ የሚለው ንብረት አልነበረም፡፡ የእኔ የሚባል ብቸኛው ንብረት ጉልበት ነበር፡፡

“ሁለት ጥያቄዎችን ይመልሱልኝ፡፡” ንጉሡ ተናገረ፣ “በዚህ ዘመን፣ መሬት ዕንቁላል የሚያህል የበቆሎ ፍሬ ማብቀል ለምን አቆመች? የልጅ ልጅዎት በሁለት ክራንቾች እገዛ፣ ልጅዎት በአንድ ክራንች እገዛ እየተራመዱ፣ እርስዎ ያለ ምንም ክራንች እንዴት ሊራመዱ ቻሉ? ዓይኖችዎ የጠሩ ናቸው፡፡ ጥርሶችዎ ጠንካራ ናቸው፡፡ ንግግርዎ ግልፅና ለጆሮ ጣፋጭ ነው፡፡ ይህ ሁሉ እንዴት ሊሆን ቻለ?”

አዛውንቱ ምላሽ ሰጡ፡-

“ይህ ሊሆን የቻለው የሰው ልጆች በራሳቸው ጉልበት መኖር አቁመው በሌሎች ጉልበት ላይ ጥገኛ ስለሆኑ ነው፡፡ በድሮ ዘመን የሰው ልጆች እንደ ፈጣሪ ሕግጋት ይኖሩ ነበር፡፡ የእነርሱ የሆነ ነገር፣ የእነርሱ ነበር፡፡ የሌሎች ምርት የራሳቸው እንዲሆን አይመኙም ነበር፡፡”

# ሦስቱ ቅዱሳን

---

በባሕር ላይ በመርከብ ወደ አንድ ገዳም ይጓዝ የነበረ ጳጳስ፣ ባሕሩ ላይ በሚገኝ ደሴት የሚኖሩ ሦስት ቅዱሳን መኖራቸው ሰማ፡፡ ቅዱሳኑን ለመጎብኘት ወስኖ፣ ይኖሩበታል ወደ ተባለው ደሴት አቀና፡፡ እንደደረሰም ሦስት እርጅና በእጅጉ የተጫጫናቸው አዛውንቶችን አገኘ፡፡ ሦስቱም አዛውንቶች ጳጳሱን እጅ ነሱ፡፡ ጳጳሱ ተናገረ፡-

"ነፍሳችሁን እየጠበቃችሁና ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሌሎች እየጸለያችሁ እንደምትኖሩ ሰማሁ፡፡ እኔ በእግዚአብሔር ቸርነት ምዕመናንን ለመጠበቅና ለማስተማር የተጠራሁ የክርስቶስ አገልጋይ ነኝ፡፡ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሆይ! እናንተን ለመጎብኘትና ለማስተማር ወደድሁ፡፡"

ሦስቱ አዛውንቶች በፈገግታ ተያዩ፡፡

"ነፍሳችሁን ለመጠበቅ ምን እንደምታደርጉና በዚህ ደሴት እግዚአብሔርን እንዴት እንደምታገለግሉ ንገሩኝ፡፡" አለ ጳጳሱ፡፡

ከሦስቱ አዛውንቶች መካከል አንደኛው ተናገረ፡-

"እግዚአብሔርን እንዴት እንደምናገለግል አናውቅም፡፡ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆይ! እኛ ራሳችንን ብቻ እናገለግላለን፡፡ እኛ ራሳችንን ብቻ እንረዳለን፡፡"

"ወደ እግዚአብሔር እንዴት ትጸልያላችሁ?" ጳጳሱ ጠየቀ

"ዘወትር ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ብለን እንጸልያለን፡- ‹‹አንተ ሦስት ነህ፣ እኛም ሦስት ነን፤ ምሕረትህ በእኛ ላይ ይሁን››" አንደኛው አዛውንት መለሰ፡፡

ሦስቱ አዛውንቶች ወደ ሰማይ አንጋጠው የዘወትር ጸሎታቸውን አሰሙ፡-

"አንተ ሦስት ነህ፣ እኛም ሦስት ነን፤ ምሕረትህ በእኛ ላይ ይሁን"

ጳጳሱ ፈገግ ብሎ ተናገረ፡-

"ስለ ሦስቱ ሥላሴዎች የሰማችሁት ነገር ቢኖርም በሥርዓቱ አልጸለያችሁም፡፡ እግዚአብሔርን ለማስደሰት እንደሻታችሁ አስተውያለሁ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔርን

እንዴት ማገልገል እንዳለባችሁ አታውቁም፡፡ ወደ እግዚአብሔር የሚጸለየው እናንተ እንደምትጸልዩት አይደለም፡፡ አዳምጡኝ! እግዚአብሔር በቅዱሳን መጻሕፍቱ የሰው ልጅ እንዴት መጸለይ እንዳለበት ያዘዘውን አስተምራችኋለሁ፡፡”

ጳጳሱ ለሦስቱ አዛውንቶች እግዚአብሔር ለሰው ልጆች እንዴት እንደተገለጸ አወሳ፡፡ ስለ አብ፣ ስለ ወልድና ስለ መንፈስ ቅዱስ ሀተተ፡፡

“ኢየሱስ የሰው ልጆችን ለማዳን ወደ ምድር መጣ፡፡ እንዴት መጸለይ እንዳለብንም አስተማረ፡፡ የምለውን እየተከተላችሁ በሉ፡- ‹‹አባታችን ሆይ››”

አንደኛው አዛውንት ጳጳሱን ተከትሎ ተናገረ፣ ‹‹አባታችን ሆይ››፤ ሁለተኛው አዛውንት ቀጠለ፣ ‹‹አባታችን ሆይ››፤ ሦስተኛው አዛውንት ተከተለ፣ ‹‹አባታችን ሆይ››

‹‹በሰማያት የምትኖር›› ጳጳሱ ቀጠለ

አንደኛው አዛውንት የጳጳሱን ንግግር ደገመ፣ ‹‹በሰማያት የምትኖር››፣ ሁለቱ አዛውንቶች ግን ‹‹በሰማያት የምትኖር›› ማለት ተሳናቸው፡፡

ጳጳሱ እንደገና ተናገረ፡- ‹‹በሰማያት የምትኖር›› ሦስቱ አዛውንቶች ጳጳሱን ተከትለው ተናገሩ፡፡

ጳጳሱ ቀኑን ሙሉ ምዕት ጊዜ እየደጋገመ እግዚአብሔር በቅዱሳን መጻሕፍቱ ያዘዘውን ጸሎት በቃላቸው እስኪያጠኑት ድረስ አስተማረ፡፡

ፀሐይ ወደ ሰገባዋ ለመሰገብ ማኮብኮብ ጀመረች፡፡ ጨረቃ የሰማይ መሬት ላይ አቆጠቆጠች፡፡

ጳጳሱ ወደ መርከቡ ለመሄድ ተነሳ፡፡ ሦስቱ አዛውንቶች የጳጳሱ እግር ሥር ወደቁ፡፡ ጳጳሱ ሦስቱን አዛውንቶች ከእግሩ ሥር አንስቶ ሳማቸው፡፡ ሠርክ እንዳስተማራቸው እንዲጸልዩ ተናግሮ ወደ መርከቡ አመራ፡፡

መርከቡ የቆመበት ቦታ ጋ እስኪደርስ የሦስቱ አዛውንቶች የጸሎት ድምፅ ከኋላ ተከተለው፡፡ መርከቡ ጎዞ ጀመረ፡፡ ደሴቱ ከጳጳሱ ዕይታ ውጭ ሆነ፡፡ ሦስቱን አዛውንቶች የአምላክን ጸሎት ያስተምር ዘንድ የላከውን እግዚአብሔር አመሥግኖ ባሕሩን በጽሞና ማስተዋል ጀመረ - ጳጳሱ፡፡ የጨረቃ ብርሃናት ፍንትውታ ያረፈበት ነጭ አብረቅራቂ ነገር ድንገት ተመለከተ፡፡ ብርሃን የሚተፋውን አብረቅራቂ ነገር በአግራሞት ተውጦ እያስተዋለ ለራሱ ተናገረ፡-

"ከኋላችን የሚቀዝፍ ጀልባ መሆን አለበት! ከአፍታ በፊት ሩቅ ነበር፡፡ አሁን በጣም ቀርቧል፡፡ ጀልባ ሊሆን አይችልም፡፡"

ጳጳሱ አብረቅራቂውን ነገር መለየት ተሳነው፡፡ ጀልባ አይደለም! ወፍ አይደለም! አሳ አይደለም!

ሦስቱ አዛውንቶች አካላቸው ብርሃን እየተፉ እጅ ለእጅ ተያይዘው በባሕሩ ላይ እየተራመዱ ወደ መርከቡ ተጠጉ፡፡

መርከቡ ጋ ሲደርሱ መናገር ጀመሩ፡-

"የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆይ! ያስተማርኸንን የእግዚአብሔር ጸሎት ረሳነው፡፡ እንደገና አስተምረን፡፡"

ጳጳሱ በጥልቅ ድንጋጤ ውስጥ ሆኖ ተናገረ፡-

"የእግዚአብሔር ሰዎች ሆይ! የራሳችሁ ጸሎት ወደ እግዚብሔር ይደርሳል፡፡ እኔ ከቶ እንዴት እናንተን ማስተማር ይቻለኛል?! ለእኛ ለኃጥአን ጸልዩ!"

ጳጳሱ ሦስቱን ቅዱሳን እጅ ነሣ፡፡

* * * * * *

"አሕዛብም በመናገራቸው ብዛት እንዲሰሙ ይመስላቸዋልና ስትጸልዩ እንደ እነርሱ በከንቱ አትድከሙ፡፡ ስለዚህ አትምሰሉአቸው፤ ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና፡፡"

ማቴ 6፥ 7-8

# አንድ ሰው ስንት ጥማድ መሬት ያስፈልገዋል?[1]

# (ተፍጻሜተ-ስግብግብ)

---

አንድ ከቀቢፀ ተስፋ ጋር የተጋባ ፓሆም የሚባል ገበሬ ነበር፡፡ ፓሆም የወፍ አዕላፍ ጥማድ መሬት ባለቤት ቢሆንም በርካሽ ዋጋ መሬት የሚሸመትበት ቅየ መኖሩን ሰማ፡፡ sማቄን ጨርቄን ሳይል መሬት በርካሽ ዋጋ ይቸበቸብበታል ወደ ተባለው ቅየ ሌት ተቀን ተጉዞ ደረሰ፡፡ እንደደረሰም ጅላጅል ከሚመስሉ የቅየው አዛውንት ጋር ድርድር ጀመረ፡፡

"ጅላጅሉ" የቅየው አዛውንት ለፓሆም አስረዱ፡- "በቀን አምስት መቶ ብር መክፈል የምትችል ከሆነ የፈለግኸውን ያህል መሬት በይዞታህ ውስጥ ማድረግ ትችላለህ፡፡"

ፓሆም የ"ጅላጅሉ"ን ንግግር ሳይረዳ ቀረ፡፡ እንዲህ ሲልም ጠየቀ፡- "‹‹ቀን›› እንዴት ያለ መገበያያ ነው? አንድ ‹‹ቀን›› ስንት ሄክታር ነው?"

"እኛ መሬት የምንገበያየው፣ እናንተ በምትገበያዩበት መንገድ አይደለም፡፡ መሬት የምንሸጠው በቀን ነው፡፡ በአንድ ቀን መራመድ የቻልኸው መሬት የአንተ ንብረት ይሆናል፡፡" አዛውንቱ ለፓሆም ጥያቄ መልስ ሰጡ፡፡

አንድ ሰው በቀን እልፍ ጥማድ መሬት መጓዝ እንደሚችል ፓሆም ተናገረ፡፡ የፓሆም ንግግር "ጅላጅሉን" አዛውንት ከልብ አሳቃቸው፡፡ "እልፍ ጥማድ መሬት ከተጓዝህ፣ እልፍ ጥማድ መሬት ይኖርሃል!" አዛውንቱ መለሱ፡፡

ሆኖም ግን አንድ ቅድመ ሁኔታ ነበር፡- ፓሆም ጉዞ የጀመረበት ቦታ ላይ ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት ካልተመለሰ ያስያዘው ገንዘብ ይወረሳል፡፡

ፓሆም እንቅልፍ አልባ ሌሊት አሳለፈ፡፡ ጎህ ሲቀድ ከቅየው ነዋሪዎች ጋር ‹‹በቀን እርምጃ›› መሬት መሸመት ወደሚጀምርበት ኮረብታ ወጣ፡፡ "ጅልጅሉ" አዛውንት የጠየቁትን አምስት መቶ ብር ኮረብታው ላይ አስቀምጦ መራመድ ጀመረ፡፡ የራሱ

---

[1] ይህ ታሪክ "What Men Live By and Other Tales" በተሰኘውና መጀመሪያ በ1885 ዓ.ም በታተመው የሊዎ ቶልስቶይ ዘመን ተሻጋሪ መጽሐፍ ውስጥ ከተካተቱት አራት ታሪኮች መካከል አንዱ ሲሆን በእጅጉ አሳጥሬ የታሪኩን መንፈስ እንዲህ ተርጉሜዋለሁ፡፡

መሬት መሆኑ ይታወቅ ዘንድ በየደረሰበት ቦታ ሁሉ ጉድጓድ መቆፈሩን ተያያዘው፡፡ መሬት ‹‹በቀን እርምጃ›› መሸመት ካሰበው በላይ ቀላል መስሎ ተሰማው፡፡ "ይህን የመሰለ ጠፍ መሬት ሊያመልጠኝ አይገባም፡፡ በርካታ ጥማድ መሬት መራመድ አለብኝ፡፡" ሲል አሰበ፡፡

ፀሐይ የሰማይ ወገብ ላይ እስከምትሠየም ድረስ ብዙ ጥማድ መሬት ተራመደ፡፡ ቀትር በነገሠ ጊዜ፣ እርምጃ ወደጀመረበት ኮረብታ ዞሮ ለመመልከት ቢሞክር ኮረብታው ከዕይታ አድማስ ውጭ ሆኖ አገኘው፡፡ ሆኖም ፓሆም ‹‹በቀን እርምጃ›› መሬት መሸመቱን አላቆመም፡፡

የሰማይ ወገብ ላይ የከተመችው ፀሐይ ሀሩር መትፋት በጀመረች ሰዓት የፓሆም የእግር ሥሮች ተቆራረጡ፡፡ ጉልበቶቹ ተብረከረኩ፡፡ እረፍት ማድረግ ቢፈልግም ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት መራመድ የጀመረበት ኮረብታ ላይ መድረስ እንዳለበት አሰበ፡፡

ፀሐይ ወደ ሰገባዋ ለመሰገብ ስታኮበኩብ፣ ፓሆም መራመድ ወደ ጀመረበት ኮረብታ በጥድፊያ መመለስ ጀመረ፡፡ በሀሩር የተሰነጣጠቁት እግሮቹ ጉዞውን አስተጓጎሉበት፡፡ ለመሮጥ በሚሞክርበት ሰዓት አልባሳቱ በላብ ዝናብ ታጠቡ፣ ሳምባው ተወተፈ፣ ልቡን ሊተፋት ደረሰ . . .

በድካም እንዳይሞት ሰጋ . . .

ምንም እንኳ ስግብግብነት የሞቱ ሰበብ እንዳይሆን ቢሰጋም፣ ሩጫውን ለመግታት አልደፈረም፡፡

የቅየው ነዋሪዎችን የማበረታቻ ድምፅ ሲሰማ የኃይሉን እንጥፍጣፊ ተጠቅሞ መሮጥ ጀመረ፡፡ ከኮረብታው እግር ሥር ሲደርስ ፀሐይ ወደ ሰገባዋ ገባች! ፓክሆም የጣር ድምፅ አሰማ፡፡ ሩጫውን መግታት ቢፈልግም ኮረብታው አናት ላይ የተሰበሰቡት የቅየው ነዋሪዎች የማበረታቻ ድምፅ አለማቆሙን ተረዳ፡፡ ፀሐይ ከኮረብታው እግር ሥር ስትታይ መጥለቋን፣ ከኮረብታው አናት ላይ ስትታይ ግን አለመጥለቋን ዐወቀ፡፡ ያለ የሌለ ኃይሉን ሰብስቦ ወደ ኮረብታው አናት መውጣት ጀመረ፡፡ ኮረብታው አናት ላይ ሲደርስ፣ "ጆላጅሉ" አዛውንት በፈገግታ ተቀበሉት፡፡

የፓሆም እግሮች ተሸነፉ . . .

ተዝለፍልፎ ወደቀ . . .

“ድንቅ ሥራ! የእልፍ ጥማድ መሬት ባለቤት ሆነሃል፡፡” አዛውንቱ ተናገሩ፡፡

የፓሆም አገልጋይ ራሱን ስቶ የተዘረረውን ፓሆም ለማንሳት ሮጠ፡፡ ፓሆም ግን በሕይወት አልነበረም፡፡ አገልጋዩ የፓሆምን መቆፈሪያ አንስቶ መቃብሩን መቆፈር ጀመረ - ለፓሆም መቀበሪያ ይሆን ዘንድ ሁለት ሜትር መሬት ቆፈረ፡፡

በርግጥም! አንድ ሰው የሚያስፈልገው የመሬት ልክ፡- ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍር ድረስ፤ ሁለት ሜትር ብቻ!!

# ሶስት ጥያቄዎች

---

ከዘመናት በአንዱ ይኖር የነበረ አንድ ንጉሥ፣ የሶስት ጥያቄዎችን መልስ ካወቀ ዳግም በችግር አረንቋ ውስጥ እንደማይዘፈቅ ተገለፀለት፡፡

ሶስቱ ጥያቄዎች እነዚህ ነበሩ፡-

እያንዳንዱን ተግባር ለመፈጸም ትክክለኛው ጊዜ መቼ ነው?

በጣም አስፈላጊ ግለሰቦች እነማን ናቸው?

ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ምንድን ነው?

ንጉሡ፣ "እነዚህን ሶስት ጥያቄዎች የሚመልስ ጠቢብ ከዕንቁ የከበረ ሽልማት ይጎናፀፋል" ሲል በግዛቶቹ ሁሉ አስነገረ፡፡ ይህን የሽልማት አዋጅ የሰሙ ምዕት ሰዎች፣ ከምዕት መልሶች ጋር ወደ ቤተ መንግሥት ነጎዱ፡፡

አንድ ጠቢብ ለመጀመሪያው ጥያቄ መልስ ይሆን ዘንድ እንዲህ ሲል ተደመጠ፡- "ንጉሡ በአግባቡ የተሰናሰለ ዝርዝር ዕቅድ ሊያበጅ ይገባዋል፡፡ ይህ ሲሆን ነው እያንዳንዱን ተግባር በትክክለኛው ጊዜ መፈጸም የሚቻለው፡፡"

ይህ ሐሳብ ያልተዋጠለት ጠቢብ፣ "ወደፊት የሚፈጸሙ ተግባራትን ተንብዮ ዕቅድ ማውጣት፣ ሱሪን በአንገት በኩል ለማውለቅ እንደመሞከር ነው፡፡ በየትኛው ጊዜ፣ የትኛው ተግባር መከናወን እንዳለበት ለማወቅ ንጉሡ እያንዳንዱን ክስተት በንቃት መከታተል አለባቸው፡፡ " ሲል ሞገተ፡፡

በመቀጠል፣ "የጠቢባን ምክር ቤት አቀቁሞ፣ በጠቢባኑ ምክር መሠረት መንቀሳቀስ" የሚል ሐሳብ ተንሸራሸረ፡፡

"ንጉሡ የሚያስፈልጋቸው የጠቢባን ምክር ቤት ሳይሆን የአስማተኞችና የትንቢት ነጋሪዎች ምክር ቤት ነው፡፡" የሚል ሐሳብም ተነሳ፡፡

ለሁለተኛው ጥያቄ የተሰጡ መልሶችም የተለያዩ ነበሩ፡፡

"በጣም አስፈላጊ ግለሰቦች የአካባቢ ገዥች ናቸው፡፡"

“የቀሳውስትንና የመነኮሳትን ያህል አስፈላጊ ግለሰቦች በንጉሡ ግዛት ውስጥ የሉም፡፡”

“ሀኪሞች ከሌሉ የሁላችን ህልውና አደጋ ላይ ስለሚወድቅ፣ በጣም አስፈላጊ ግለሰቦች እነርሱ ናቸው፡፡”

“ንጉሡ እምነታቸውን ማሳደር ያለባቸው በጦረኞች ላይ ነው፡፡”

ለሁለተኛው ጥያቄ የተሰጡ መልሶች ነበሩ፡፡

ለሶስተኛው ጥያቄም በርካታ መልሶች ተሰነዘሩ፡፡ ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል ተብለው ከተጠቀሱት ውስጥ ሳይንስ፣ ሃይማኖትና የጦርነት ጥበብ ዋና ዋናዎቹ ሆኑ፡፡

ለሶስቱ ጥያቄዎች የተሰጡት ሁሉም መልሶች የንጉሡን ቀልብ መግዛት ባለመቻላቸው “ከዕንቁ የከበረው” ሽልማት ያለ ተሸላሚ ቀረ፡፡

ከአያሌ ማሰላሰል በኋላ፣ ንጉሡ በተራራ ላይ የምናኔ ሕይወት የሚመራን ጠቢብ ለመጎብኘት ወሠነ፡፡ መናኙ ጠቢብ በእንግድነት የሚቀበለው ያጡ የነጡ ተመፅዋቾችን ብቻ እንደሆነና ከባለጠጎችና ከባለሥልጣናት ጋር መገናኘትን አጥብቆ እንደሚጠየፍ ንጉሡ ያውቃል፡፡ ይሁን እንጂ የሶስቱ ጥያቄዎችን መልስ አጥብቆ በመሻቱ፣ ራሱን ደብቆና ተራ ገበሬ መስሎ ወደ መናኙ ጠቢብ ለመሄድ ተነሳ፡፡ ተከታዮቹን ከተራራው ሥር እንዲጠብቁት አዝዞ፣ መናኙ ጠቢብ የከተመበትን ረዥም ተራራ መውጣት ጀመረ፡፡

ከሰዓታት ፍለጋ በኋላ፣ መናኙን ጠቢብ ከጎጆው ፊት ለፊት በሚገኝ የአትክልት ስፍራ ውስጥ ሲቆፍር አገኘው፡፡ እንግዳውን የተመለከተው መናኙ ጠቢብ፣ ራሱን በማወዛወዝ ሰላምታ ካቀረበለት በኋላ ቁፋሮውን ቀጠለ፡፡መናኙ ጠቢብ መቆፈሪያውን በሰነዘረ ቁጥር የሚያሰማው ድምፅ፣ በቁፋሮው መዳከሙን ያሳብቃል፡፡ ንጉሡ ወደ መናኙ ጠቢብ ቀርቦ መናገር ጀመረ፡- “ለሶስት ጥያቄዎች መልስ ይሰጡኝ ዘንድ ሌት ተቀን ተጉዤ መጣሁ፡- እያንዳንዱን ተግባር ለመፈጸም ትክክለኛው ጊዜ መቼ ነው? በጣም አስፈላጊ ግለሰቦች እነማን ናቸው? ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ምንድን ነው?”

መናኙ ጠቢብ ንጉሡን በፅሞና አዳመጠው፡፡ መልስ ለመስጠት ግን አልደፈረም፡፡ ወደ ቁፋሮው ተመለሰ፡፡ “የደከመዎት ይመስላሉ፤ ልርዳዎ፡፡” ንጉሡ ተናገረ፡፡ መናኙ ጠቢብ ንጉሡን አመሥግኖ መቆፈሪያውን አስረከበው፡፡ ንጉሡ መቆፈር ጀመረ፡፡

ሁለት ጉድጓዶችን እንደቆፈረ፤ ቁፋሮውን አቋርጦ ሶስቱ ጥያቄዎችን በድጋሚ ለመናኙ ጠቢብ አቀረበ፡፡ አሁንም መናኙ ጠቢብ መልስ ለመስጠት አልደፈረም፡፡

“እረፍት ውሰድ፡፡ ወደ ቁፋሮ መመለስ እችላለሁ፡፡” አለ መናኙ ጠቢብ ወደ መቆፈሪያው እየጠቆመ፡፡

ንጉሡ ቁፋሮውን ማቋረጥ አልፈለገም፡፡ መቆፈሩን ተያያዘው፡፡ ሰዓታት ነጎዱ፡፡ ፀሐይ በተራራው አናት ሥር ተሸሸገች . . . . .

“ብዙ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጬ የመጣሁት ለሶስቱ ጥያቄዎች መልስ ይሰጡኛል በሚል ተስፋ ነበር፡፡ መልስ ሊሰጡኝ ካልፈቀዱ ጨለማው ከመበርታቱ በፊት ወደ ጎጆዬ ልመለስ፡፡” አለ ንጉሡ፤ መቆፈሪያውን ተደግፎ፡፡

መናኙ ጠቢብ ካቀረቀረበት ቀና ብሎ እንዲህ ሲል ጠየቀ፡-

“የሚያቃስት ሰው ድምፅ ይሰማሃል?”

የንጉሡና የመናኙ ጠቢብ ዓይኖች፣ ረዥም ነጭ ሪዝ ያንዠረገገ ሽማግሌ ከጫካው ውስጥ ብቅ ሲል ተመለከቱ፡፡ ከጫካው ውስጥ ብቅ ያለው ሽማግሌ፣ አውሎ ንፋስ እንደሚያወዛውዛት ባሕር ዛፍ አንዴ ወደ ቀኝ፣ አንዴ ወደ ግራ ይንከላወሳል፡፡ እጆቹ በደም የጨቀየ ሆዱ ላይ አርፈዋል፡፡ ሽማግሌው እያቃሰተ መሬት ላይ ተዘረረ፡፡ ንጉሡና መናኙ ጠቢብ ራሱን ስቶ የተዘረረውን ሽማግሌ ልብሶች በማውለቅ ላይ ሳሉ ሽማግሌው በፅኑ መቁሰሉን ተረዱ፡፡ ንጉሡ የሽማግሌውን ቁስል በጥንቃቄ ማፅዳት ጀመረ፡፡ የራሱን ልብስ አውልቆ የሽማግሌውን ቁስል አሰረለት፡፡ የሚፈስሰው ደም እስኪቆም ድረስ ንጉሡ የተቻለውን ሁሉ አደረገ፡፡

በመጨረሻም የቆሰለው ሽማግሌ ራሱን አወቀ፡፡ የሚጠጣው ውኃ ማግኘት ይችል እንደሆነ ጠየቀ፡፡ ንጉሡ በአቅራቢያው ወደሚገኝ ምንጭ ገሰገሰ፡፡ ውኃ በቅል ቀድቶ ተመለሰ፡፡

ጨለማው የሚዳሰስ ሆነ፡፡ የምሽቱ ብርድም በረታ . . .

ንጉሡና መናኙ ጠቢብ ተባብረው የቆሰለውን ሽማግሌ ወደ መናኙ ጠቢብ ጎጆ አስገቡት፡፡ የመናኙ ጠቢብ አልጋ ላይ አስተኙት፡፡

ንጉሡ ተዳክሟል፡፡ እንጥፍጣፊ ኃይል አልነበረውም፡፡ ገና ጎኑን ከማሳረፉ በእንቅልፍ ባሕር ውስጥ ሰጠመ፡፡ ንጉሡ ከእንቅልፍ ሲነቃ፣ ፀሐይ ከተራራው አናት ሥር መብቀል

ጀምሯ ነበር፡፡ ወደ መናኙ ጠቢብ አልጋ ሲመለከት፣ የቁስለኛው ሽማግሌ ዓይኖች በግርታ ሲመለከቱት ያዛቸው፡፡

“ንጉሥ ሆይ! ይቅር ይበሉኝ!” አለ ቁስለኛው ሽማግሌ፤ በተዳከመና በሚቆራረጥ ድምፅ፡ ፡

“ምን እኩይ ግብር ሠራህና ነው ይቅር የምልህ?” ንጉሡ ጠየቀ፡፡

“ንጉሥ ሆይ! እርስዎ አያውቁኝም፡፡ እኔ ግን አውቅዎታለሁ፡፡ጠላትዎ ነበርሁ፡፡ ባለፈው ጦርነት ወንድሜን ገድለው ሀብት ንብረቴን ስለወረሱ ልገድልዎ ምዬ ተገዝቼ ነበር፡፡መናኙን ጠቢብ ለመገናኘት ወደ ተራራው ብቻዎን እንደሚወጡ በሰማሁ ጊዜ የሚመለሱበትን ሰዓት ጠብቄ ልገድልዎ ተዘጋጀሁ፡፡ ለበርካታ ሰዓታት እስኪመለሱ ብጠብቅም ላገኝዎ አልቻልሁም፡፡

እርስዎን ለመፈለግ ወስኜ ከተደበቅሁበት ምሽግ ወጣሁ፡፡ ነገር ግን ከተራራው ሥር በሰፈሩት ተከታዮችዎ እጅ ወደቅሁ፡፡ጠላትዎ እንደሆንኩና ልገድልዎ እንደተዘጋጀሁ አወቁ፡፡ ክፉኛ አቆሰሉኝ፡፡ እንደ ዕድል ሆኖ አመለጥሁ፡፡ እርስዎንና መናኙን ጠቢብ አገኘሁ፡፡ እርስዎን ባላገኝ ኖሮ በሕይወት አልኖርም ነበር፡፡ ልገድልዎ አሰብሁ፤ እርስዎ ግን ሕይወቴን ታደጓት! በሥራዬ አፈርሁ! ከዚህ ቁስል ተፈውሼ በሕይወት መቆየት የምችል ከሆነ ዕድሜ ልኬን ሳገለግልዎ እኖራለሁ፡፡ ልጅና የልጅ ልጆቼም እርስዎን ሲያገለግሉ ይኖራሉ፡፡ ንጉሥ ሆይ! ይቅር ይበሉኝ!”

ንጉሡ ከቀድሞ ጠላቱ ጋር ይቅር በመባባሉ ተደሰተ፡፡ የተወረሰውን ንብረት ሊመልስለት ቃል ገባ፡፡ ቁስለኛው ሽማግሌ ከቁስሉ እስከሚፈወስ ድረስ የራሱን ሀኪሞችና አገልጋዮች እንደሚልክለት ገለፀ፡፡ ቁስለኛውን ሽማግሌ ወደ ቤቱ እንዲወስዱት ተከታዮቹን አዝዞ ወደ መናኙ ጠቢብ አመራ፡፡ ወደ ቤተ መንግሥት ከመመለሱ በፊት ለመጨረሻ ግዜ ሶስቱ ጥያቄዎቹን ለመጠየቅ ወስኗል፡፡ መናኙን ጠቢብ በአትክልት ስፍራው ውስጥ በተቆፈሩት ጉድጓዶች ዘር እየበተነ አገኘው፡፡

“ጥያቄዎችህ በሙሉ ተመልሰዋል፡፡” አለ መናኙ ጠቢብ ንጉሡን በአትኩሮት እያጤነ፡፡

“እንዴት?” አለ ንጉሡ ግራ በተጋባ ድምፀት፡፡

“ትላንት በቁፋሮ መዳከሜን ዓይተህ ባትረዳኝ ኖሮ ወደ ቤተ መንግሥት በምትመለስበት ሰዓት ቁስለኛው ሽማግሌ ይገድልህ ነበር፡፡ ከእኔ ጋር ባለመቆየትህ ክፉኛ ትፀፀት ነበር፡፡ ስለዚህ ትክክለኛው ጊዜ በአትክልት ስፍራው ውስጥ የቆፈርክበት

ሰዓት ነበር፡፡ በጣም አስፈላጊው ግለሰብ እኔ ነበርሁ፡፡ ልዩ ትኩረት የሚሻው ተግባር ደግሞ እኔን መርዳት ነበር፡፡ በኋላም ቁስለኛው ሽማግሌ እኛ ጋር በደረሰ ጊዜ፣ ከቁስሉ የሚፈሰው ደም እንዲቆም ጥረት ያደረክበት ሰዓት ትክክለኛው ጊዜ ነበር፡፡ ምክንያቱም ጥረት ባታደርግ ኖሮ ቁስለኛው ሽማግሌ ሊሞት ይችል ስለነበር፣ ዕርቀ ሠላም ሳታወርዱ ትቀሩ ነበር፡፡ በተመሳሳይ፣ ቁስለኛው ሽማግሌ በጣም አስፈላጊ ግለሰብ ነበር፡፡ ቁስሉን መንከባከብ ደግሞ ልዩ ትኩረት የሚሻ ተግባር፡፡

ልብ በል! ሁሌም አንድ አስፈላጊ ሰዓት አለ፡፡ እርሱም “አሁን” ነው! በእኛ ቁጥጥር ሥር ያለ ብቸኛው ሰዓት “አሁን” ነው፡፡ ሁልጊዜም በጣም አስፈላጊው ግለሰብ “አሁን” አጠገብህ ያለው ሰው ነው፡፡ ልዩ ትኩረት የሚሻው ተግባር ደግሞ አሁን አጠገብህ ያለውን ሰው ማስደሰት መቻል!”